# ከተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ወደ ሌሎች የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች የሚደረግ የተሳታፊ ጎልማሶች የሽግግር መመሪያ ቁጥር 85/2013

Transition Guide for Participating Adults from Integrated Activity-Based Adult Education to Other Education and Training Programs (Directive No. 85/2013)

ትምህርት ሚኒስቴር
Ministry of Education

ኅዳር 1፥ 2013

# ማውጫ

**ይዘት**
**ገጽ**


1. መግቢያ………………………………………………………………………………………… …………………..2
2. የመመሪያዉ አስፈላጊነት……………………………………………………………………………………… ….3
3. ዓላማ…………………………………………………………………………………………… …………………….3
4. በመመሪያዉ ዉስጥ የተካተቱ ቃላት ትርጓሜዎች……………………………………………………………4
5. የሽግግር መመሪያዉ ታሳቢ ያደረጋቸዉ ጉዳዮች ……………………………………………………………5
6. ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት ……………………………………………………………………..5

6.1. የምዘና አሰጣጥ ስርዓት……………………………………………………………………………………..5

6.2. የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ስርዓት……………………………………………………………………6

7. የሽግግር ሂደት…………………………………………………………………………………………… ……….7

7.1. ወደ መደበኛ/አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የሚደረግ ሽግግር……………………..7

7.2. ወደ መደበኛ ያልሆነ ቴክኒክና ሙያ ትምርትና ስልጠና የሚደረግ ሽግግር…………………….8

7.3. ወደ ድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም የሚደረግ ሽግግር…….8

8. በምዘና ፣ በምስክር ወረቀት አሰጣጥና በሽግግር ሂደቱ የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት….9

8.1. የአመቻች ተግባርና ኃላፊነት…………………………………………………………………………….9

8.2. የመማማሪያ ጣቢያ ኃላፊ/የት/ቤት ርዕሰ መምህር ተግባርና ኃላፊነት.............................10

8.3. የቀበሌ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት................................................10

8.4. የጉድኝት ሱፐርቫይዘር ተግባርና ኃላፊነት..........................................................................11

8.5. የቀበሌ የጎልማሶች ትምህርት ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት.......................................11

8.6. የዞን/የክፍለ ከተማ /የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት...................................11

8.7. የወረዳ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት..............................11

8.8. የዞን/የክፍለ ከተማ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት...........12

8.9. የክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት............................................13

8.10. የክልል/የክፍለ ከተማ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት.......13

8.11. የፌደራል የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት..........................14

9. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች.............................................................................................................14

## 1. መግቢያ

በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዱ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች የጎልማሶች ትምህርት አንዱ ነው። ዕቅዱ በሀገራችን ያለውን ዕድገት ሁሉን አቀፍ ለማድረግ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን ተደራሽ በማድረግ ዕድሜያቸው ከ15-60 ዓመት የሚገኙ ወጣቶችና ጎልማሶች ከዕለት ኑሮአቸው ጋር የተገናኘ የህይወት ክህሎት በማስጨበጥ ህይወታቸውን እንዲያሻሽሉ በማድረግ ለአገር ኢኮኖሚ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማስቻል ነው።

በመሆኑም ይህንን ግብ ለማሳካት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት መርሐ ግብር ተነድፎ በመተግበር ላይ ይገኛል፡፡ ለዚህም ሀገር አቀፍ የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂ በ2000 ዓ.ም

ተቀርፆ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም በተጠናከረና በተቀናጀ መልኩ እንዲተገበር ላለፉት ዓመታት ትምህርት ሚኒስቴር ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ከዚህም ባሻገር የጎልማሶች ትምህርት ስትራቴጂን በሥራ ለመተርጎም የሚያግዙ የተለያዩ የመነሻ ሰነዶች ተዘጋጅተዋል፡፡ ሰነዶቹ ጎልማሶች ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን አዳብረው በሀገር ልማት በስፋት እንዲሳተፉ ለማስቻል ከክልል ትምህርት ቢሮዎች፣ ከትምህርት ባለሙያዎችና ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር ተዘጋጅተው በመተግበራቸው በተሳታፊ ጎልማሶች ህይወት ላይ ተጨባጭ ለውጦች እየተመዘገቡ ይገኛል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፕሮግራሙ ሁለት ዓመት ትግበራ መጠናቀቅን ተከትሎ ከፕሮግራሙ ተሳታፊ ጎልማሶች ፍላጎት በመነሳት፣ ፕሮግራሙን ከዕድሜ ልክ ትምህርት(Lifelong Learning) ጽንሰ ሀሳብ ጋር ለማስተሳሰር እንዲሁም የፕሮግራሙን ጥራትና ተገቢነት ለማስጠበቅ ከተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ወደ ሌሎች የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች የሚደረግ የተሳታፊ ጎልማሶች የሽግግር መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበታል፡፡ በመሆኑም መመሪያውን ለማዘጋጀት ባለድርሻ አካላት ያሳተፈ ግብረ ኃይል ከትምህርት ሚኒስቴር ከጐልማሶችና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ማስተባበሪያ፣ ከሥርዓተ ትምህርት ዝግጅትና ትግበራ ዳይሬክቶሬት፣ ከቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ኤጀንሲና በፕሮግራሙ ዙሪያ በቅርበት ከሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በተለይም ከጀርመን የጎልማሶች ትምህርት ማኀበር የምስራቅ አፍሪካ ሪጅናል ጽ/ቤት(Dvv-international) የተውጣጡ ባለሙያዎች ተቋቁሞ ፕሮግራሙ ያለበትን ሁኔታና የተሳታፊ ጎልማሶችን ቀጣይ የትምህርት ፍላጎት አስመልክቶ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡ በጥናቱ ግኝትና በተሰጡት የመፍትሔ ሀሳቦች መነሻነት ይህ መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

በመሆኑም በዚህ ሰነድ ውስጥ የመመሪያው አስፈላጊነት፣ የመመሪያው ዓላማዎች፣ በመመሪያው ውስጥ የተካተቱ ቃላትና ሐረጋት ትርጓሜዎች፣ ምዘናና የምስክር ወረቀት፣ የሽግግር ሂደት እና የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት፣እንዲሁም ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች የሚሉ ርዕሰ ጉዳዮች ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

## 2. የመመሪያው አስፈላጊነት

የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም መተግበር ከተጀመረ ከ2003 ዓ.ም ጀምሮ የሁለት ዓመቱን የመማማር ሂደት ያጠናቀቁ ጎልማሶች በምን መልኩ እና ከየትኛው የመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ጋር ተመጣጣኝ እንደሚሆን የሚገልጽ መመሪያ ስላልነበር በፕሮግራሙ የተነሳሳው የጎልማሶች የትምህርት ፍላጎት ቀጣይነት ሳይወሰን ቆይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት የፕሮግራሙን ጠቀሜታ የተረዱ ጎልማሶችም በቀጣይ በሌሎች የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች በመቀጠል የትምህርት ፍላጎታቸውን ለማርካት በተደጋጋሚ ጥያቄ ሲያነሱ ቆይተዋል፡፡ ይህንን

የጎልማሶች ጥያቄ የሚመልስ መመሪያ ባለመኖሩ ትምህርታቸውን መቀጠል የሚፈልጉ ጎልማሶች በምንና እንዴት መስተናገድ እንዳለባቸው ለክልሎችም አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡

ስለሆነም እነዚህን ጥያቄዎች ሊመልስ ወይም ችግሮችን ሊፈታ የሚችልና የትምህርት ለሁሉምና የምዕተ ዓመቱን የልማት ግቦች ለማሳካት የበኩሉን አስተዋጽኦ ሊያበረክት የሚችል የሽግግር መመሪያ ማዘጋጀቱ አስፈላጊ መሆኑ ስለታመነበት ይህ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም የሽግግር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

## 3. ዓላማ

### 3.1. አጠቃላይ ዓላማ

የሁለት ዓመቱን ተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁ ጎልማሶች ወደ ተለያዩ የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች የሚሸጋገሩበትን ግልጽ አቅጣጫ ለማመላከት ሲሆን ዝርዝር ዓላማዎችም የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 3.2. ዝርዝር ዓላማዎች

- ጎልማሶች የሁለት ዓመቱን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ሲያጠናቅቁ ወደ መደበኛው/አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ወይም ወደ መደበኛ ያልሆነ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ወይም ወደ ድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም እንዲሸጋገሩ ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር ለሰው ኃይል አቅም ግንባታ አስተዋጽኦ ለማድረግ፣
- በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም እና በሌሎች የትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራሞች መካከል ያለውን ግንኙነት በማጠናከር የትምህርትና ሥልጠና ዕድልን ለማስፋት፣
- በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ግልጽና ወጥነት ያለው የሽግግር ሥርዓት ለመዘርጋት፣
- የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ጥራትና ተገቢነት ለማስጠበቅ፣ እንዲሁም ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ፣

## 4. በመመሪያው ውስጥ የተካተቱ ቃላት ትርጓሜዎች

4.1. **የሽግግር መመሪያ፡** ማለት ከተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ወደ መደበኛ/አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ወይም መደበኛ ያልሆነ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና ወይም ድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራሞች የሚደረገውን ሽግግር የሚመለከት መመሪያ ነው፡፡

4.2. **የአተገባበር መመሪያ**፡ ማለት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም የአተገባባር መመሪያ ነው፡፡

4.3. **ተቋም**፡ ማለት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ለመደገፍ ከሚመለከታቸው መንግስታዊ አካላት ጋር ስምምነት በማድረግ ጎልማሶችን መዝግቦ በማስተማር ላይ የሚገኝን አገር በቀል ወይም የዓለም አቀፍ የልማት ድርጅትን/የሃይማኖት ተቋማትን የሚመለከት ነው፡፡

4.4. **ጎልማሶች**፡ ማለት ዕድሜያቸው ከ15-60 ዓመት የሆኑ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተሳታፊዎችን የሚመለከት ነው፡፡

4.5. **ፕሮፋይል**፡ ማለት ጎልማሶች በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተሳትፈው ሊያመጡ የሚጠበቅባቸውን ሁለንተናዊ የባሕርይ ለውጥ የሚመለከት ነው፡፡

4.6. **መደበኛ ያልሆነ ቴክኒክና ሙያ ትምህርት ሥልጠና**፡ ማለት ከመደበኛው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ፕሮግራም ውጪ የሆኑ አጫጭር የሙያ ሥልጠናዎችን የሚመለከት ነው፡፡

4.7. **ድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም**፡ ማለት የሁለት ዓመቱን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁ ጎልማሶች በፕሮግራሙ የቀሰሙትን ዕውቀትና ክህሎት በዘላቂነት የሚጠቀሙበትና ቀጣይ ትምህርታቸውን የሚከታተሉበት ራሱን የቻለ አንዱ ፕሮግራም ነው፡፡

4.8. **የትብብር ሥልጠና**፡ ማለት መደበኛ ባልሆነው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ፕሮግራም የሚሳተፉ ጎልማሶች በሚሰለጥኑበት የሙያ መስክ ከሚሠሩ በድርጅቶች/ኢንዱስትሪዎች/ ጋር ተመድበው እየሠሩና በድርጅቶች/ኢንዱስትሪው/ ድጋፍ እየተደረገላቸው ተግባራዊ ክህሎትና ዕውቀት የሚቀስሙበት የሥልጠና አሰጣጥ ዘዴ ነው፡፡

4.9. **አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት**፡ ማለት እድሜያቸው ለትምህርት ደርሶ በተለያዩ ምክንያቶች መደበኛ ትምህርት ቤት መግባት ላልቻሉ ልጆች በአመራጭነት የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ እርከን ትምህርት (1-4 ክፍሎች) በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ የሚማሩበት ፕሮግራም ነው፡፡

4.10. **ጣቢያ**፡ ጣቢያ ማለት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች የሚከታተሉ ጎልማሶች የሚማማሩበት ማዕከል ማለት ነው፡፡

4.11. **የጉድኝት ሱፐርቫይዘር**፡ ማለት በተወሰነ ቅርበት ያላቸው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ስራ በጋራ የሚያስተባብር ባለሙያ (ሱፐርቫይዘር) ማለት ነው፡፡

## 5. የሽግግር መመሪያው ታሳቢ ያደረጋቸው ጉዳዮች፣

የሽሽግግር መመሪያ ዝግጅት ታሳቢ ያደረጋቸዉ የሚከተሉትን ጉዳዮች ነዉ፡

5.1. የዜጎችን የመማር መብት ማስከበርና ከዚህም ጋር ተያይዞ ሰዎች በዕድሜ ሳይገደቡ በሕይወት ዘመናቸዉ በሙሉ ትምህርትና ስልጠና ማግኘት የሚገባቸዉ መሆናቸዉ፣

5.2. ጎልማሶች የሚማሩትና ዉጤታማ የሚሆኑት በሙሉ ፈቃደኝነትና ፍላጎት እንደመሆኑ የሁለት አመቱን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁ ጎልማሶች ባሳዩት ከፍተኛ ፍላጎት መሰረት ቀጣይ ትምህርትና ስልጠና የሚያገኙበትን እድሎች ማመቻቸት አስፈላጊ መሆኑ፣

5.3. ጎልማሶች በተለያየ የኑሮ ዉጣ ዉረድ ያለፉ በአይነቱና በመጠኑ በርካታ የሆነ ተሞክሮ ወይም ገጠመኝ ( Experience) ክምችት ባለቤት በመሆናቸዉ በመማማር ሂደት ዉስጥ በትምህርት ተቀባይነት ብቻ ሳይሆን የትምህርት ምንጭና ሰጪም መሆን የሚችሉ መሆናቸው፡

5.4. ጎልማሶች ለመማማር ያላቸዉ ዝግጁነት በአካላዊ እድገት ወይም ከሌላ ተጽእኖ የመነጨ/የሚመነጭ ብቻ ሳይሆን ከአጠቃላይ ልማትና እድገት እንዲሁም ከማህበራዊ ተግባር፣ሃላፊነትና ግዴታ የሚመነጭ መሆኑን፣

5.5. ጎልማሶች ከማንምና ከምንም ጥገኝነት ነጻ የሆኑ ማለትም ራሳቸዉን የቻሉ በመሆናቸዉ በራሳቸው የመተማመን (self confidential) ስሜትና ዝንባሌ ያላቸዉ መሆኑን፣

5.6. ጎልማሶች ስለ ጊዜ ያላቸዉ አመለካከት የተለየ ማለትም የጊዜን ዉስንነትና ጠቀሜታን ጠንቅቀዉ የሚገነዘቡ መሆኑ፣

5.7. ጎልማሶች የሚማማሩት በመምህር መራሽ ስልት ሳይሆን በተሳታፊ ተኮር የመማማር ስልት መሆኑን፣

5.8. ትምህርታቸዉን በመደበኛ ት/ቤት ለሚቀጥሉት ጎልማሶች በእንግሊዘኛና በሂሳብ ትምህርቶች የተለየ እገዛ ሊደረግላቸው የሚገባ መሆኑ፣ እና

5.9. ለመደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ስለ ጎልማሶች ልዩ ባህሪያትና የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ኦሬንቴሽን (Orientation) ሊደረላቸው የሚገባ መሆኑ ናቸው፡፡

# 6. ምዘናና የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት

## 6.1.የምዘና አሰጣጥ ሥርዓት

6.1.1 በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት የአተገባበር መመሪያ በተቀመጡ የምዘና ዘዴዎች መሠረት በአመቻቾች ተከታታይ ምዘና ይሰጣል፡፡

6.1.1. የተሳታፊ ጎልማሶች የዕለት ተዕለት የመማማር እንቅስቃሴያቸውንና በተለያዩ የምዘና ዘዴዎች በመጠቀም የተገኘውን ተከታታይ የምዘና ውጤት መረጃ/ፖርትፎሊዮ/ በእያንዳንዱ/ዷ ተሳታፊ ስም በመማማሪያ ጣቢያ ደረጃ ይደራጃል፡፡

6.1.2. የእያንዳንዱ/ዷ ተሳታፊ ጎልማሳ የተከታታይ የምዘና ውጤት መረጃ ማለትም ወደ መማማሪያ ጣቢያ አዘውትሮ መምጣትን፣ ሰዓት ማክበርን፣ በንቃት መሳተፍን፣ የማንበብ፣ የመጻፍና ማስላት ክህሎት ከጊዜ ወደ ጊዜ የሚያሳየው መሻሻል፣ በምልከታ በተዘጋጀው ቼክሊስት መሠረት የተመዘገበ በህይወቱ/ቷ ያመጣው/ችው ለውጥ፣ ራስን የመግለጽ ችሎታ፣ ሁሉ የሚያጠቃልል ነው፡፡

6.1.3. የምዘና ሥርዓቱ በተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት አጥጋቢ የብቃት መለኪያ የተቀመጡትን ፕሮፋይሎች መሠረት ያደረገ ነው፡፡

6.1.4. የምዘና መስፈርቱ የእያንዳንዱ/ዷ ተሳታፊ ጎልማሳ የተከታታይ የምዘና ውጤት መረጃ 30%፣ በቀበሌ ቴክኒክ ኮሚቴ የሚካሄድ ምልከታ 20%፣ በተሳታፊ ጎልማሶች የሚካሄድ ግምገማ (Peer Evaluation)10%፣ የተሳታፊ ጎልማሳ የራስ ግምገማ (Self Evaluation) 10%፣ የጽሑፍ ምዘና(የማንበብ፣ የመጻፍና የማስላት ክህሎት ምዘና) 30% ይሆናል፡፡

6.1.5. የጽሑፍ (የማንበብ፣የመጻፍና የማስላት ክህሎት) ምዘና ጥያቄ በቀበሌ ቴክኒክ ኮሚቴና በአመቻቹ/በአመቻቿ የሚዘጋጅ ይሆናል፡፡

6.1.6. የሁለት ዓመቱን ትምህርት በአንድ ዓመት ለማጠናቀቅ አቅምና ችሎታ ያላቸዉ ተሳታፊ ጎልማሶች የመማማር ሂደቱን ቢያንስ ለ432 ሰዓታት ተከታትሎ ሲያጠናቅቁ የጽሁፍ ምዘና በወረዳ ደረጃ ይሰጣል፡፡

6.1.7. የጽሑፍ (የማንበብ፣የመጻፍና የማስላት ክህሎት)ምዘና ከመሰጠቱ በፊት ምዘናው የሚካሄድበት ጊዜ አስቀድሞ ለተሳታፊዎች በማስታወቂያ ሠሌዳና በአመቻቾቹ በኩል ይገለጻል፤ እንዲሁም የ30 ቀናት የዝግጅት ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

6.1.8. የጽሑፍ ምዘና ውጤት በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ ለተሳታፊ ጎልማሶች ይገለጻል፡፡

## 6.2. የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሥርዓት

6.2.1. የአንደኛ ዓመት የመማማር ሂደቱን (ቢያንስ 216 ሰዓታት) ሲያጠናቅቁና የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት አጥጋቢ የብቃት መለኪያ መሠረት የሚጠበቀውን ፕሮፋይል ማሟላታቸው ( ማንበብ መጻፍና ማስላት መቻላቸዉን) ሲረጋገጥ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

6.2.2. የአንደኛ ዓመት የመማማር ሂደቱን ለሚያጠናቅቁ ተሳታፊ ጎልማሶች የሚሰጠው የምስክር ወረቀት በዓመቱ ውስጥ በመማማሪያነት የቀረቡት ይዘቶችን ( ማንበብ መጻፍና ማስላት መቻላቸዉን) የሚገልጽ ይሆናል፡፡

6.2.3. የሁለተኛ ዓመት የመማማር ሂደቱን (ቢያንስ 216 ሰዓታት) ማጠናቀቃቸው ሲረጋገጥ ለሁለተኛ ዓመት ተሳታፊ ጎልማሶች የምስክር ወረቀት ይሰጣል፤የሚሰጠውም የምስክር ወረቀት በዚህ መመሪያ በተራ ቁጥር 5.1.5 በተገለጹት የምዘና መስፈርቶች ተመዝኖ 50% እና ከዚያ በላይ ውጤት ላመጡ ተሳታፊዎች ይሆናል፡፡

6.2.4. የሁለት ዓመቱን ትምህርት በአንድ ዓመት ለማጠናቀቅ አቅምና ችሎታ ያላቸዉ ተሳታ ጎልማሶች የመማማር ሂደቱን ቢያንስ ለ432 ሰዓታት ተከታትለው ሲያጠናቅቁና በወረዳ ደረጃ የሚሰጠዉን የጽሁፍ ምዘና ማለፋቸዉ ሲረጋገጥ የምስክር ወረቀት ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

6.2.5. የሚሰጠው የምስክር ወረቀት በመደበኛው/አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ያለውን አቻ የክፍል ደረጃ ወይም መደበኛ ባልሆነው የቴክኒክና ሙያ ሥልጠና መሳተፍ የሚያስችል መሆኑንም የሚገልጽ ይሆናል፡፡

6.2.6. የምስክር ወረቀቱ ሕጋዊ ማስረጃ ሊሆን የሚችለው በጣቢያ ኃላፊው የተፈረመና በቀበሌው የሚገኝ/የመማማሪያ ጣቢያውን በበላይነት የሚቆጣጠረው/ ትምህርት ቤት ወይም ትምህርቱን የሰጠው ተቋም ማህተም ያረፈበት ከሆነ ብቻ ነው፡፡

# 7. የሽግግር ሂደት

## 7.1. ወደ መደበኛ/አመራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም የሚደረግ ሽግግር

7.1.1. በዚህ መመሪያ በተራ ቁጥር 5.2.1 በተገለጸው መሠረት የ1ኛ ዓመት የመማማር ሂደቱን (ቢያንስ 216 ሰዓታት) ስለማጠናቀቃቸዉ የምስክር ወረቀት ያገኙ ተሳታፊ ጎልማሶች በመደበኛዉ ትምህርት ፕሮግራም በ2ኛ ክፍል ገብተዉ ትምህርታቸዉን ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡

7.1.2. በዚህ መመሪያ በተራ ቁጥር 5.2.1 በተገለጸው መሠረት የ1ኛ ዓመት የመማማር ሂደቱን (ቢያንስ 216 ሰዓታት) ስለማጠናቀቃቸዉ የምስክር ወረቀት ያገኙ ተሳታፊ ጎልማሶች በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ደረጃ አንድ ገብተዉ ትምህርታቸዉን ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡

7.1.3. በዚህ መመሪያ ቁጥር 5.2.3 በተገለጸው መሰረት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ስለማጠናቀቃቸው የምስክር ወረቀት ያገኙ ተሳታፊ ጎልማሶች በመደበኛው ትምህርት ፕሮግራም ሶስተኛ ክፍል ገብተው ትምህርታቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡

7.1.4. በዚህ መመሪያ በተራ ቁጥር 5.2.3 በተገለጸው መሠረት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ስለማጠናቀቃቸው የምስክር ወረቀት ያገኙ ተሳታፊ ጎልማሶች በሶስት ዓመት የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ደረጃ ሁለት ገብተው ትምህርታቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡

7.1.5. ችሎታ፣አቅምና ጊዜ ኖሯቸዉ የሁለት ዓቱን ትምህርት በ አንድ ዓመት ውስት የሚጨርሱ ጎልማሶች በወረዳ ደረጃ የሚሰጣቸዉን የጽሁፍ ምዘና ያለፉና የምስክር ወረቀት ያገኙ ተሰታፊ ጎልማሶች በመደበኛው ትምህርት ቤት ሶስተኛ ክፍል ገብተዉ ትምህርታቸዉን ሊከታሉ ይችላሉ፡፡

7.1.6. ችሎታ፣አቅምና ጊዜ ኖሯቸዉ የሁለት ዓመቱን ትምህርት በ አንድ ዓመት ውስጥ የሚጨርሱ ጎልማሶች በወረዳ ደረጃ የሚሰጣቸዉን የጽሁፍ ምዘና ያለፉና የምስክር ወረቀት ያገኙ ተሰታፊ ጎልማሶች በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ሶስተኛ ክፍል ገብተዉ ትምህርታቸዉን ሊከታሉ ይችላሉ፡፡

8.7.11. የሁለት ዓመቱን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁ ጎልማሶች በድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተመዝግበው እንዲከታተሉ ለቀበሌው ትምህርትና ሥልጠና ቦርድ አመራር ይሰጣል፡፡

## 8.8. የዞን/የክፍለ ከተማ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

8.8.1. ምዘናው በመመሪያው መሠረት በአግባቡ ስለመካሄዱ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

8.8.2. የምዘና ውጤት መረጃውን አጠናቅሮ ይይዛል፣ ለክልል ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴም ይልካል፡፡

8.8.3. የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደቱ በመመሪያው መሠረት በሁሉም ወረዳዎች/ቀበሌዎች ስለመተግበሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

8.8.4. በሁሉም ወረዳዎች መደበኛ ባልሆነው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላት መቀጠል ፈልገው ወደ ሥልጠና ማዕከላቱ የሚመጡ ጎልማሶችን በሚያቀርቡት የምስክር ወረቀት መሠረት ተቀብሎ በሚፈልጉት የሙያ መስክ ሥልጠና እንዲያገኙ አመራር ይሰጣል፡፡

8.8.5. የዞኑ/የክፍለ ከተማው ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ጽ/ቤትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጽ/ቤት በዞኑ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆነው ለሥልጠና ማዕከላቱ አስፈላጊውን የቴክኒክና የግብአት ድጋፍ ያደርጋሉ፣ለሠልጣኞች የትብብር ሥልጠና እንዲያገኙ አመራር ይሰጣሉ፡፡

8.8.6. ለድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም የማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ወይም የንባብ ቤቶች በየቀበሌው እንዲደራጁ ለወረዳዎች አመራር ይሰጣል፣ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ እንዲሁም የሚያስፈልጉ ግብአቶች እንዲሟሉ ይሠራል፡፡

8.8.7. የሁለት ዓመቱን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁ ጎልማሶች በድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተመዝግበው እንዲከታተሉ ለወረዳዎች አመራር ይሰጣል፡፡

## 8.9. የክልል/ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ተግባርና ኃላፊነት

8.9.1. ወደ መደበኛ ትምህርት ቤቶች/በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማዕከላት ለሚገቡ ጎልማሶች የተሟላ የመማር-ማስተማር ሂደት እንዲኖር አስፈላጊውን እገዛና የግብአት አቅርቦት እንዲደረግላቸው አመራር ይሰጣል፣ ክትትል ያደርጋል፡፡

8.9.2. ለድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም የማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ወይም የንባብ ቤቶች በየቀበሌው እንዲደራጅ አመራር ይሰጣል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፣አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

7.1.7. በዚህ መመሪያ በተራ ቁጥር 5.2.3 በተገለጸው መሠረት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ስለማጠናቀቃቸው የምስክር ወረቀት ያገኙ ተሳታፊ ጎልማሶች በመደበኛው/አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ተመዝግበው ትምህርታቸውን ሊቀጥሉ የሚችሉት የምስክር ወረቀቱ ከተሰጣቸው ጊዜ ጀምሮ በአሥራ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ ብቻ ይሆናል፡፡ ይህም የሆነበት ዋና ምክንያት ጎልማሶች በሁለት ዓመቱ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም የቀሰሙትን መሠረታዊ የማንበብ፣የመጻፍና የማስላት ክህሎት ሳይረሱት ወደ መደበኛው/አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ተመዝግበው ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ ለማስቻል ሲሆን አስራ ስድስት ወራት እንዲሆን የተወሰነበት ምክንያት ለጎልማሶች በቂ የመመዝገቢያ ጊዜ እንዲያገኙ ታሳቢ ተደርጎ ነው፡፡ ሆኖም ግን በፕሮግራሙ በ2005 ዓ.ም፤በ2006 እና በ2007 ዓ.ም አጠናቀው ስለማጠናቀቃቸው የምስክር ወረቀት ያገኙ ሆነው ነገር ግን ይሕ የሽግግር መመሪያ ፀድቆ ስራ ላይ ሳይውል በመዘግየቱ ምክኒያት በመደበኛው/አማርጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ተመዝግበው ትምህርታቸውን ሊቀጥሉ ያልቻሉ ጎልማሶች በአስራ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በሚለው ሳይገደቡ በመደበኛ/በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ተመዝግበው ትምህርታቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡

7.1.8. የምስክር ወረቀት በተሰጣቸው በአሥራ ስድስት ወራት ጊዜ ውስጥ በመደበኛ/አማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ቤት ሳይመዘገቡ ጊዜው ያለፈባቸው ጎልማሶች የጽሑፍ ምዘና በድጋሚ ወስደው 50% እና ከዚያ በላይ ውጤት ካስመዘገቡ የምስክር ወረቀት ሊሰጣቸውና ተመዝግበው ትምህርታቸውን ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡

## 7.2. ወደ መደበኛ ያልሆነ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና የሚደረግ ሽግግር

**7.2.1.** በዚህ መመሪያ በተራ ቁጥር 5.2.3 በተገለጸው መሠረት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ስለማጠናቀቃቸው የምስክር ወረቀት ያገኙ ተሳታፊ ጎልማሶች ወደ መደበኛ ያልሆነ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላት ተሸጋግረው በአጫጭር ሥልጠናዎች መሠልጠን ይችላሉ፡፡

## 7.3. ወደ ድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም የሚደረግ ሽግግር

የድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም/Post-IFAE/ ዋና ዓላማ ጎልማሶች በሁለት ዓመቱ ፕሮግራም የቀሰሙትን ዕውቀትና ክህሎት ማስቀጠልና የመሃይምነትን ግርሻ መከላከል ነው፡፡

ለዚህም በየአካባቢው የማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ወይም የንባብ ቤቶች ይደራጃሉ፣ የአካባቢውን ኅብረተሰብ ፍልጎት መሠረት ባደረጉ የተለያዩ ጭብጦች ላይ በተለያዩ ቋንቋዎች የአካባቢ ጋዜጦች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ መጽሄቶች... በማዘጋጀት በንባብ ቤቶች ተጠቅምጠው የንባብ አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡ በተጨማሪም ፕሮግራሙን በአግባቡ ለመተግበር እንዲቻል

በየደረጃው ያሉ የጎልማሶች ትምህርት ባለሙያዎች፣ የጎልማሶች ትምህርት ቴክኒክ ኮሚቴ አባላትና እንዲሁም አመቻቾች በድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም አመራርና አተገባበር ላይ ሥልጠና ይሰጣቸዋል፡፡

ፕሮግራሙ ካሉት ፋይዳዎች ዋና ዋናዎቹ፡-

- የማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ወይም የንባብ ቤቶችን በመጠቀም የኅብረተሰቡን የንባብ ባህል ማዳበር፣ እንዲሁም የንባብ ቤቶችን በባህል ማዕከልነትና በመወያያ ስፍራነት እንዲያገለግሉ በማደረጃት የዲሞክራሲ ባህልን ማጠናከር፣ በንባብ ቤቶች በኩል ጎልማሶች ወቅታዊ መረጃ እንዲያገኙ ማስቻል፣
- በአጠቃላይ ጎልማሶች በማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላት ወይም በንባብ ቤቶች በመገኘት የማንበብ ወይም ተንቀሳቃሽ የንባብ ቤቶችን በማደራጀት፣ የመጻፍ፣ የማስላትና የሕይወት ክህሎታቸውን በማሳደግ በዘላቂነት እንዲጠቀሙበት በማስቻል በአገሪቱ በመካሄድ ላይ ያለውን ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ልማትና እድገት ለማፋጠን ድርሻቸውን እንዲወጡ ማድረግ የፕሮግራሙ ፋይዳዎች ናቸው፡፡ ስለሆነም፡-

7.3.1. በዚህ መመሪያ በተራ ቁጥር 6.2.3 በተገለጸው መሠረት የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ስለማጠናቀቃቸው የምስክር ወረቀት ያገኙ ተሳታፊ ጎልማሶች በድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡

7.3.2. የድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ዝርዝር አተገባበር በተመለከተ በቀጣይ በትምህርት ሚኒስቴር ማንዋል/Implemenetation Guideline/ የሚዘጋጅ ሲሆን ማንዋሉም የፕሮግራሙን ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ፣ የሥልጠና አሰጣጥ ሥርዓት፣ የሚወስደውን ጊዜና የሚኖሩትን ደረጃዎች፣ የሚያስፈልጉትን አደረጃጀቶችና ግብአቶች፣ እንዲሁም የክትትልና ድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓት የሚያካትት ይሆናል፡፡

## 8. በምዘና፣ በምስክር ወረቀት አሰጣጥና በሽግግሩ ሂደት የባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

### 8.1. የአመቻች ተግባርና ኃላፊነት

8.1.1. የተሳታፊ ጎልማሶችን ስም ዝርዝርና ሌሎች መረጃዎችን መዝግቦ ይይዛል/መዝግባ ትይዛለች፡፡

8.1.2. ለእያንዳንዱ/ዷ ተሳታፊ ጎልማሳ የተከታታይ ምዘና ውጤት መረጃ ያደራጃል/ታደራጃለች፡፡

8.1.3. የጎልማሶችን የዕለት ተዕለት የመማማር እንቅስቃሴያቸውንና በተማማሩት መሠረት ያከናወኑትን ተግባራት በመከታተል የተከታታይ ምዘና ውጤት መረጃ መዝግቦ ይይዛል/መዝግባ ትይዛለች ፤ ውጤትም ይሰጣል/ትሰጣለች፡፡

8.1.4. የተሳታፊ ጎልማሶችን የአቻና የራስ ግምገማ የሚካሄድበትን ሁኔታ ያመቻቻል/ታመቻቻለች፤ የግምገማ ሂደቱን ይመራል/ትመራለች፤ ውጤቱንም መዝግቦ ይይዛል/መዝግባ ትይዛለች፡፡

8.1.5. የጽሑፍ (የማንበብ፣ የመጻፍና የማስላት ክህሎት) ምዘና የሚሰጥበትን ጊዜ ከተሳታፊ ጎልማሶች ጋር በመሆን ይወስናል/ትወስናለች፤ ስለጽሑፍ ምዘና አሰጣጡ ሂደትም ከቀበሌ ቴክኒክ ኮሚቴ አባላት ጋር በመነጋገር የጽሑፍ ምዘናው እንዲሰጥ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡

8.1.6. የጽሑፍ ምዘና ወረቀቱን በማረም ውጤቱን መዝግቦ ይይዛል/መዝግባ ትይዛለች፡፡

8.1.7. የተሳታፊ ጎልማሶችን የጽሑፍ ምዘና ውጤት መረጃውን መዝግቦ ይይዛል/መዝግባ ትይዛለች፡፡

8.1.8. የእያንዳንዱን ተሳታፊ ጎልማሳ የምዘና ውጤት ማጠቃለያ በማዘጋጀት በጣቢያው ኃላፊ እንዲረጋገጥ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡

8.1.9. በዚህ መመሪያ ተራ ቁጥር 6.2.1 በተገለጸው መሠረት ቢያንስ 216 ሰዓታት ተከታትለው ያጠናቀቁ የአንደኛ ዓመት ተሳታፊ ጎልማሶችን ዝርዝር ለጣቢያ ኃላፊ ያቀርባል/ታቀርባለች፡፡

8.1.10. በዚህ መመሪያ በተራ ቁጥር 6.2.4 በተገለጸው መሠረት ቢያንስ 216 ሠዓታት ያጠናቀቁና በምዘና መስፈርት መሠረት 50% እና ከዚያ በላይ ውጤት ያመጡ ተሳታፊ ጎልማሶችን ለይቶ/ለይታ ለጣቢያ ኃላፊ ያቀርባል/ታቀርባለች፡፡

## 8.2. የመማማሪያ ጣቢያ ኃላፊ/የት/ቤት ርዕሰ መምህር ተግባርና ኃላፊነት

8.2.1. የጎልማሶች የተከታታይ የምዘና ውጤት መረጃ/ፖርትፎሊዮ/ ተደራጅቶ እንዲያዝ ለአመቻቾች የቅርብ ክትትልና እገዛ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡

8.2.2. በተራ ቁጥር 5.1. መሠረት የሚካሄደውን የምዘና ሂደት ከአመቻቹ/ከአመቻቿ ጋር በመሆን ያስተባብራል/ታስተባብራለች፡፡

8.2.3. ከአመቻቹ/ከአመቻቿ ጋር በመሆን የጽሑፍ ምዘና ለተሳታፊ ጎልማሶች እንዲሰጥ የቀበሌ ቴክኒክ ኮሚቴውን ያስተባብራል/ታስተባበራለች፡፡

8.2.4. የእያንዳንዱ/ዷ ተሳታፊ ጎልማሳ የምዘና ውጤት ማጠቃለያ በአመቻቹ/በአመቻቿ ተዘጋጅቶ ሲያቀርብ ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ ለቀበሌው የቴክኒክ ኮሚቴ አቅርቦ ያጸድቃል/አቅርባ ታጸድቃለች፡፡

8.2.5. በዚህ መመሪያ በተራ ቁጥር 6.2.1 እና 6.2.3 በተገለጸው መሠረት በእያንዳንዱ ዓመት ቢያንስ 216 ሠዓታት ያጠናቀቁና በምዘና መስፈርት መሠረት 50% እና ከዚያ በላይ ውጤት ያመጡ ተሳታፊ ጎልማሶች ዝርዝር በአመቻቾች ሲቀርብለት/ላት የምስክር ወረቀት በማዘጋጀት የምስክር ወረቀቱ ላይ ይፈርማል/ትፈርማለች፤ እንዲሁም በቀበሌው የሚገኝ/የመማማሪያ ጣቢያውን በበላይነት የሚቆጣጠረው/ትምህርት ቤት ወይም ትምህርቱን በሰጠው ተቋም ማህተም በማረጋገጥ ለተሳታፊዎች ይሰጣል/ትሰጣለች፡፡

8.2.6. በመደበኛ ትምህርት/በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም መቀጠል ፈልገው ወደ ትምህርት ቤቱ የሚመጡ ጎልማሶችን በሚያቀርቡት የምስክር ወረቀት መሠረት በመቀበል እንዲመዘገቡ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡

8.2.7. በትምህርት ቤቱ/በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማዕከሉ ተመዝግበው ትምህርት የጀመሩ ጎልማሶች አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል/ታመቻቻለች፡፡

## 8.3. የቀበሌ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

8.3.1. ትምህርታቸውን በመደበኛ/አማራጭ መሰረታዊ ትምህርት መቀጠል ለሚፈልጉ ጎልማሶች በቀበሌው ካሉ ትምህርት ቤቶች ጋር በመተባበር ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

8.3.2. መደበኛ ባልሆነው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላት መቀጠል ፈልገው ወደ ሥልጠና ማዕከላቱ የሚመጡ ጎልማሶችን በሚያቀርቡት የምስክር ወረቀት መሠረት ተቋሙ ተቀብሎ እንዲመዘግባቸውና በሚፈልጉት የሙያ መስክ ሥልጠና እንዲያገኙ ድጋፍ ያደርጋል፡፡

8.3.3. መደበኛ ባልሆነው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላት የሚሰጠውን ሥልጠና አፈጻጸሙን ይከታተላል፤አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡

8.3.4. ለድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም የማኅበረሰብ የመማማሪያ ማዕከላትን ወይም የንባብ ቤቶችን ያደራጃል፤ እንዲሁም የሚያስፈልጉ ግብአቶችን እንዲሟሉ ይሠራል፡፡

8.3.5. የሁለት ዓመቱን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ያጠናቀቁ ጎልማሶች በድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም ተመዝግበው እንዲከታተሉ ያደርጋል፡፡

## 8.4. የጉድኝት ሱፐርቫይዘር ተግባርና ኃላፊነት

8.4.1. በየመማማሪያ ጣቢያዎች ለሚካሄደው የምዘና አሰጣጥ ሂደት ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል/ታደርጋለች፡፡

8.4.2. የተከታታይ የምዘና ውጤቶች መረጃ በአግባቡ ተመዝግቦ መያዙን ያረጋግጣል/ታረጋግጣለች፡፡

## 8.5. የቀበሌ የጎልማሶች ትምህርት ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

8.5.1. ለተሳታፊ ጎልማሶች የሚሰጠውን የጽሑፍ ምዘና ከአመቻቾች ጋር በመሆን ያዘጋጃል፤ የምዘና መልሶችንም አዘጋጅቶ ለአመቻቹ ይሰጣል፡፡

8.5.2. ለጽሑፍ ምዘና ዝግጅት የሚያስፈልገውን ግብአት ያቀርባል፡፡

8.5.3. በተ.ራ ቁጥር 5.1.4. እና 5.1.5. በተጠቀሰው መሠረት ተሳታፊ ጎልማሶች በሕይወታቸው ያመጡትን ለውጥ በየቤታቸው በመሄድና ምልከታ በማካሄድ ውጤት ይሰጣል፡፡

8.5.4. በጣቢያው ኃላፊ የሚቀርብለትን የተሳታፊ ጎልማሶች የምዘና ውጤት ያጸድቃል፡፡

8.5.5. የጸደቀውን የምዘና ውጤት አጠናቅሮ ለወረዳው ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ይልካል፡፡

8.5.6. የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደቱን በበላይነት ይከታተላል፤ይቆጣጠራል፡፡

## 8.6. የዞን/የክፍለ ከተማ/የወረዳ ትምህርት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

8.6.1. በዞኑ/በክ/ከተማው/በወረዳው ያሉ መደበኛ ትምህርት ቤቶች/በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማዕከላት በመደበኛ ትምህርት/በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም መቀጠል ፈልገው ወደ ትምህርት ቤቱ/ማዕከሉ የሚመጡ ጎልማሶችን ተቀብሎ ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ አመራር ይሰጣል፡፡

8.6.2. ወደ መደበኛ ትምህርት ቤቶች/በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ማዕከላት ለገቡ ጎልማሶች በመማር ማስተማር ሂደት አስፈላጊውን እገዛና የግብአት አቅርቦት እንዲደረግላቸው አመራር ይሰጣል፣ ክትትልም ያደርጋል፡፡

8.6.3. አስፈላጊውን በጀት በመመደብ ለድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም እንዲስፋፋ ያደርጋል፡፡

## 8.7. የወረዳ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

8.7.1. ምዘናው በመመሪያው መሠረት በአግባቡ ስለመካሄዱ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

8.7.2. ለምዘና የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ለወረዳው/ለቀበሌው ያቀርባል፡፡

8.7.3. የሁለት ዓመቱን ትምህርት በአንድ ዓመት ለማጠናቀቅ አቅምና ችሎታ ያላቸዉ ተሳታፊ ጎልማሶች የመማማር ሂደቱን ቢያንስ ለ432 ሰዓታት ተከታትሎ ሲያጠናቅቁ የጽሁፍ ምዘና በማዘጋጀት ምዘናዉ በወረዳ ደረጃ እንዲሰዋ ይደረጋ፡፡

8.7.4. ከቀበሌ ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ጸድቆ የተላከለትን የምዘና ውጤት መረጃ አጠናቅሮ ይይዛል፤ያደራጃል፡፡

8.7.5. የምዘና ውጤት መረጃውን አጠናቅሮ ለዞን/ለክፍለ ከተማ/ክልል ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ይልካል፡፡

8.7.6. ለተሳታፊ ጎልማሶች የሚሰጠውን የምስክር ወረቀት አሳትሞ ለቀበሌዎችና መማማሪያ ጣቢያዎች ያሠራጫል፡፡

8.7.7. በምስክር ወረቀት አዘገጃጀትና የአሰጣጥ ሂደት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን ድጋፍ ያደርጋል፡፡

8.7.8. መደበኛ ባልሆነው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላት መቀጠል ፈልገው ወደ ሥልጠና ማዕከላቱ የሚመጡ ጎልማሶችን በሚያቀርቡት የምስክር ወረቀት መሠረት ተቀብሎ በሚፈልጉት የሙያ መስክ ሥልጠና እንዲያገኙ አመራር ይሰጣል፡፡

8.7.9. የወረዳው ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ጽ/ቤትና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ጽ/ቤት በወረዳው የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆነው ለሥልጠና ማዕከላቱ አስፈላጊውን የቴክኒክና የግብአት ድጋፍ ያደርጋሉ፤ለሠልጣኞች የትብብር ሥልጠና እንዲያገኙ ያመቻቻሉ፡፡

8.7.10. ለድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም የንባብ ቤቶች በየቀበሌው እንዲደራጁ ለቀበሌው ትምህርትና ሥልጠና ቦርድ አመራር ይሰጣል፤ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፣ እንዲሁም የሚያስፈልጉ ግብአቶች እንዲሟሉ ይሠራል፡፡

8.9.3. በክልሉ/ከተማ አስተዳደሩ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ምዘና፣ የምስክር ወረቀት አሰጣጥና ከሽግግር ሂደት ጋር ተያያዥነት ያለውን የመረጃ ፍሰት ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡

## 8.10. የክልል/ከተማ አስተዳደር የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

8.10.1. ምዘናው በመመሪያው መሠረት በአግባቡ ስለመካሄዱ ለዞን/ለክፍለ ከተማ/ወረዳ ቴክኒክ ኮሚቴ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

8.10.2. የምዘና ውጤት መረጃውን አጠናቅሮ ይይዛል፤ ለፌደራል ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴም ይልካል፡፡

8.10.3. የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደቱ በመመሪያው መሠረት በሁሉም ዞኖች/ክፍለ ከተሞች/ወረዳዎች ስለመተግበሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

8.10.4. የሁለት ዓመቱን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ፕሮግራም አጠናቀው ወደ መደበኛ ባልሆነው የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ማዕከላት የሚመጡ ጎልማሶችን በሚፈልጉት የሙያ መስክ ሥልጠና እንዲያገኙ አመራር ይሰጣል፡፡

8.10.5. የክልሉ/የከተማ አስተዳደሩ ቴክኒክና ሙያ ሥልጠና ኤጀንሲ በክልሉ/በከተማ አስተዳደሩ የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ አባል ሆኖ አመራር ይሰጣል፤ ለሥልጠና ማዕከላቱ አስፈላጊውን የቴክኒክና የግብአት ድጋፍ ያደርጋል፤ አፈጻጸሙንም ይከታተላል፡፡

## 8.11. የፌደራል የጎልማሶች ትምህርት ቦርድ/ቴክኒክ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት

8.11.1. ምዘናው በመመሪያው መሠረት በአግባቡ ስለመካሄዱ ለክልል/ለከተማ አስተዳደር ቴክኒክ ኮሚቴ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

8.11.2. ከየክልሎች/ከተማ አስተዳደሮች የምዘና ውጤት መረጃ በመሰብሰብ አጠናቅሮ ይይዛል፡፡

8.11.3. የምስክር ወረቀት አሰጣጥ ሂደቱ በመመሪያው መሠረት በሁሉም ክልሎችናከተማ አስተዳደሮች ስለመተግበሩ ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፡፡

8.11.4. የሽግግር መመሪያው በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወጥነት ባለው መንገድ ተግባራዊ እንዲሆን አቅጣጫ ይሰጣል፤ ክትትል ያደርጋል፤ የቴክኒክና ሙያ ድጋፍ ይሰጣል፡፡

8.11.5. ከሽግግር መመሪያው አተገባበርና አፈጻጸም አኳያ የባለድርሻ አካላትን አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፡፡

# 9. ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

9.1. ልዩ ተሰጥኦ ያላቸውና ይህም በአመቻቹ/ቿ በጣቢያ ኃላፊው/ኃላፊዋ የተመሰከረላቸው ተሳታፊ ጎልማሶች በመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ከ3ኛ ክፍል በላይ መግባት ሲፈልጉ በትምህርት

ቤቶች የመግቢያ ፈተና ተሰጥቶ በሚያገኙት ውጤት መሠረት በትምህርት ቤቱ የሚወሰን ይሆናል፡፡

9.2. በመደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ትምርታቸውን ለሚቀጥሉ ጎልማሶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት እንደ አዲስ ስለሚጀምሩና የሂሳብ ትምህርትን ያልተረዱቸው ጽንሰ ሀሳቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ስለሚገመት የ1ኛና የ2ኛ ክፍል የእንግሊዝኛ ቋንቋና የሂሳብ ትምህርት ከ3ኛ ክፍል ትምህርት ጋር ተጣጥሞ እንዲሰጣቸው የሚደረግበት ስልት በክልል ደረጃ እንዲቀየስ ተደርጎ በትምህርት ቤቶች እንዲተገበር ይደረጋል፡፡

9.3. በአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ለሚቀጥሉ ጎልማሶች የእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት እንደ አዲስ ስለሚጀምሩ የሂሳብ ትምህርትን ያልተረዱቸው ጽንሰ ሀሳቦች ሊኖሩ እንደሚችሉ ስለሚገመት የደረጃ አንድ የእንግሊዝኛ ቋንቋና የሂሳብ ትምህርት ከደረጃ ሁለት ትምህርት ጋር ተጣጥሞ እንዲሰጣቸው የሚደረግበት ስልት በክልል ደረጃ እንዲቀየስ ተደርጎ በማዕከላቱ ልዩ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

9.4. ቁጥራቸው ለአንድ ክፍል የሚሆኑ ጎልማሶች ሲመዘገቡ ከጎልማሶች ባሕርይና ከሚጠይቀው ክህሎት አንጻር ራሱን በቻለ ክፍል ለብቻቸው እንዲማሩ ቢደረግ ይመረጣል፡፡

9.5. ለመደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ስለጎልማሶች ባህርያትና የትምህርት አቀራረብ ገለጻ (Orientation) ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

9.6. የአንድ ዓመቱን ተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ፕሮግራም ቢያንስ ለ216 ሰዓታት ተከታትለው ነገር በሚሰጣቸዉ ምዘና ከ50% በታች ያመጡ ተሳታፊ ጎልማሶቸ በድጋሚ ተመዝግበው እንዲማማሩ ይደረጋል፡፡

9.7. የሁለት ዓመቱን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት አጠናቀው በምዘና ውጤታቸው ከ50% በታች ያመጡ ተሳታፊ ጎልማሶች በፍላጎታቸው መሠረት በተጨማሪ የመማማሪያ ሰዓት በማመቻቸት አጥጋቢ ውጤት እንዲያመጡ በማስቻል የምስክር ወረቀት እንዲሰጣቸው ይደረጋል፡፡

9.8. ይህ መመሪያ ከመዉጣቱና በስራ ላይ እንዲውል ከመደረጉ በፊት የሁለት ዓመቱን የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማች ትምህርት ፕሮግራም አጠናቀው የተመረቁ ጎልማሶች በዚህ መመሪያ ተ.ቁ 6.1.4 በተገለጸው መሰረት የጽሁፍ ምዘና በድጋሚ ወስደው 50% እና ከዚያ በላይ ዉጤት ካስመዘገቡ የምስክር ወረቀት ሲሰጣቸዉ በመደበኛዉ ትምህርት ወደ ሶስተኛ ክፍል ወይም በአማራጭ መሰረታዊ ትምህርት ፕሮግራም ወደ ደረጃ ሁለት ተሸጋግረው ሊማሩ ይችላሉ፡፡

9.9. የድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት ሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ በቀጣይ ይዘጋጃል፡፡

9.10. በመደበኛው ትምህርት ፕሮግራም በቀኑ የትምህርት ፕሮግራም መማማር ለማይችሉ ጎልማሶች ትምህርታቸውን በማታው ክፍለ ጊዜ እንዲማሩ ሁኔታዎች ሊመቻቹ ይገባል፡፡

9.11. የሴቶችንና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተሳታፊ ጎልማሶች በተመከለተ በሌሎች መመሪያዎች የተቀመጡት የማበረታቻና ድጋፍ ደንቦች በዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

9.12. መመሪያው አሁን ባለው የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርት አፈጻጸም ላይ ተመስርቶ የተዘጋጀ መመሪያ ስለሆነ በቀጣይ ሊኖር በሚችለው የፕሮግራሙ አፈጻጸም ላይ ተመስርቶ ሊሻሻል ይችላል፡፡

9.13. በከተማ ቀበሌዎችና በገጠር ቀበሌዎች ያሉት የፕሮግራሙ ተጠቃሚዎች ፍላጎት በዳሰሳ ጥናቱ እንደታየው የተለያየ በመሆኑ በከተማ አካባቢዎች ወደ መደበኛ ትምህርት ለመግባት ያለውን ሰፊ ፍላጎት ለማሟላት በቂ ዝግጅት ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን በገጠራማ ቀበሌዎች የድህረ የተቀናጀ ተግባር ተኮር የጎልማሶች ትምህርትን በበቂ ሁኔታ ለማዳረስም እንዲሁ በቂ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

9.14. መደበኛ ያልሆነ ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት በአብዛኛው የሚገኙት በከተማ አካባቢ እንደመሆኑ በዚህ ፕሮግራም በአጫጭር የሙያ ሥልጠናዎች መሳተፍ የሚፈልጉትን ጎልማሶች ለመድረስ የግብርና ሙያ ማሰልጠኛ ማእከላትንና ሌሎች ሳተላይት ጣቢያዎችን ማቋቋም የሚቻልበትን ቅንጅታዊ አሰራር መፍጠር ተገቢ በመሆኑ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡